በስደት ላይ ያለው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጽ/ቤት

THE LEGITIMATE HOLY SYNOD OF THE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH MAIN OFFICE IN EXILE

Date: 05/11/2018
Ref. No:14/05/2018

*«የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥
ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ፥
ስቃያቸውንም አውቄአለሁ።» (ዘጸአት 3፥7)*

# ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራውና በስደት የሚገኘው፤ ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፤ ከግንቦት 1-3 ቀን 2010 ዓ.ም (May 9-11, 2018) በካሊፎርኒያ፤ ሳንሆዜ መካነ ራማ ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ካቴድራል 47ኛውን የርክበ ካህናት ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ አካሂዷል። የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ትምህርተ ሃይማኖትን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንንና ወቅታዊውን የአገራችንና የቤተ ክርስቲያናችንን ሁኔታ አስመልክቶ፤ በስፋት ከተወያየ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥቷል።

1) የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ የሆነው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ በመዋቅራዊ አደረጃጀት፣ በሰው ኃይል፣በስብከተ ወንጌል፣ በተለያዩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲሁም በገንዘብና በቁሳቁስ አቅም ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና በሀገረ ስብከትና በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ደረጃም አስፈላጊው ተደራሽነት እንዲኖረው በማድረግ፤ ሐዋርያዊ ተልእኮውን በተሻለ ብቃትና ቅልጥፍና ለማከናወን በሚያስችሉት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ተወያይቶ፤ በቅርቡ በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን በርካታ የመፍትሔ ሐሳቦችንና ጠቃሚ ውሳኔዎችን አስተላልፏል።

2) እንደሚታወቀው ቅድስት አገራችን ኢትዮጵያ የሦስት ሺህ ዘመን አኩሪ ታሪክ ያላት ታላቅ ሀገር ናት። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በረጅሙ ጉዞዋ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ፤ ለዘመናት ተከብሮና ተጠብቆ የኖረውን ብሔራዊ ነጻነቷንና የሕዝቧን አንድነት የሚፈታተኑ በርካታ ተግዳሮቶችን በማስተናገድ ላይ ትገኛለች። በመሆኑም የአገራችንና የሕዝባችን ባለአደራ የሆነው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ፤ በግፍ ከተሰደደበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ሩብ ምዕት ዓመት ባስቆጠረው ከባድ መከራ ውስጥ ካለው ሕዝባችን ጎን በመቆም የአንድነትና የፍቅር፣ የሰላምና የፍትሕ ድምጹን፤ ከጸሎተ ምሕላ አዋጅ ጋር በተደጋጋሚ ሲያሰማ ቆይቷል።

ስለሆነም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ «የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ፥ ስቃያቸውንም አውቄአለሁ» (ዘጸ. 3፥7) ተብሎ እንደተጻፈ፤ እነሆ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ በመላው አገራችንና በውጭው ዓለም በስደት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፤ በአንድነት የጮኹትን ጩኸት ሰምቶ፣ በምልዓት የተፈጸመውን ግፍና ሰቆቃ አይቶ እንዲሁም በከንቱ የፈሰሰውን

የንጹሐን ዜጎችን እንባና ደም ተመልክቶ አገራችንና ሕዝባችንን በረድኤት ሊጎበኝ ሥራ መጀመሩን የሚጠቁሙ ተስፋ ሰጭ ምልክቶችን በማየቱ፤ የተሰማውን ደስታ ይገልጣል። ከሁሉ አስቀድሞ ይህንን የተስፋ ቀን ለአገራችንና ለሕዝባችን በቸርነቱ ላዘጋጀ፤ ቸር አምላክ ክብርና ምስጋናን ያቀርባል። በመቀጠልም የዛሬው ብሩህ ተስፋ ጭላንጭል እንዲታይ፤ «ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት» ለተሰኘው ታላቅና ክቡር ዓላማ ስትሉ፤ ከፍተኛ መሥዋዕትነት የከፈላችሁና እየከፈላችሁም ያላችሁ፤ በአገር ውስጥና በውጭው ዓለም የምትገኙ ውድ ኢትዮጵያውን ወገኖቻችን፤ የአባቶችን አምላክ እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይክፈላችሁ፣ እንባችሁን ያብስላችሁ፣ ከኃዘናችሁ ያጽናናችሁ፣ እያልን ቸሩ አምላክ ከድካማችሁ በኃያል ክንዱ ያበረታችሁ ዘንድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ትጸልያለች።

ከዚህም ጋር ላለፉት ዐሥርት ዓመታት በአገራችን ሰፍኖ የቆየው ኢሰብአዊና ኢፍትሐዊ የመንግሥት ሥርዓት እንዲለወጥና በምትኩም ሁሉን አቀፍ ሥርዓት እንዲመሠረት በአጽንኦት የሚያሳስበው፤ በቅርቡ በአሜሪካ ምክር ቤት የተዘጋጀውና «HR128» በመባል የሚታወቀው ሰነድ እንዲጸድቅ ለተባበራችሁ ሁሉ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል። ይልቁንም የቃል ኪዳን ሕዝቡን የሚጠብቅበትና የሚታደግበት ጥበቡ ረቂቅና ድንቅ የሆነው አምላክ፤ ለሕዝበ እሥራኤል ነጻነት መሪ የሆነውን ሙሴ፤ ከገዳያቸው ፈርዖን ቤተ መንግሥት ውስጥ እንዳስነሣላቸው፤ ዛሬም በሕዝባችን ላይ ከባዱን የአገዛዝ ቀንበር ከጫነው አካል መካከል የተማሩና የሚያገናዝቡ፣ በሳልና አስተዋይ፣ አርቆ አሳቢ፣ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የሚታይባቸው፣ በኢትዮጵያና በሕዝቧ አንድነት የሚያምኑ፣ ለሕዝባችን ተደራሽና ተስፋ ሰጭ የሆኑ መሪ በማስነሣቱ ቸርነቱን ፍጹም እናደንቃለን።

በተለይም በሀገረ አሜሪካ «የእናቶች ቀን» በሚከበርበት በዚህ ታሪካዊ ሳምንት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አቢይ አህመድ በወላጅ እናታቸው አንጻር ከባዱን የቤተሰብ ቀንበር ተሸክመው፤ የኅብረተሰባችን የጀርባ አጥንትና የአገራችን ምሰሶ ለሆኑ እናቶች፤ ልዩ ዕውቅናና ክብር በይፋ ሲሰጡ ማየታችንንና መስማታችንን ስናስታውስ መልካም አርአያነታቸውን እናደንቃለን። በዚህ አጋጣሚ የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ማዕከል በሆነው ሀገረ አሜሪካ ለምትገኙ ውድ ኢትዮጵያውያት እናቶች በሙሉ «መልካም የእናቶች ቀን» እንዲሆንላችሁ ቅዱስ ሲኖዶስ ልባዊ ምኞቱን ይገልጣል።

አዲሱ የአገራችን ጠቅላይ ሚኒስትር በቁርጠኝነት የጀመሩትን መሠረታዊ የሰላምና የፍቅር፤ የአንድነትና የአብሮነት፤ የይቅርታና የዕርቅ እንዲሁም የብሔራዊ መግባባት አጀንዳዎች አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪያችንን እያቀረብን፤ የጀመሩት መልካም ውጥን ከፍጻሜ እንዲደርስና መልካም ፍሬያቸውን በጋራ ለማየት እንዲያበቃን መልካም ምኞታችንና የዘወትር ጸሎታችንም ነው። በዚህ አጋጣሚ ሳንጠቅስ የማናልፈው ዐቢይ ነጥብ ቢኖር፤ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አማራጭ ሐሳቦችንና የተሻሉ መርሐ ግብሮችን በማቅረባቸው ብቻ «ተቃዋሚ» በሚል አሉታዊ አገላለጽ ተፈርጀው የቆዩት ወገኖች «ተፎካካሪ» በሚል አወንታዊ አመለካከት መታየታቸውና ብሔራዊ አጀንዳዎቻቸውን ይዘው በመቅረብ፤ በጋራ ለመወያየት ጥሪ መደረጉ በራሱ ትልቅ እርምጃ መሆኑን ነው። ስለሆነም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም የምትገኙ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣የሰብአዊ መብት ተሚጋቾች እንዲሁም የሲቪክ ማኅበራት የተሰጠውን ዕድል በመጠቀም ልዩነታችሁን ተቀራርባችሁ በውይይት በመፍታት፤ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና በሕዝባችሁ አንድነት ላይ በንቃትና በትጋት እንድትሠሩ፤

ከምንጊዜውም በበለጠ ወቅቱ የሚጠይቀው ተቀዳሚና ዐቢይ ተግባር መሆኑን፤ ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንዖት ያሳስባል። ይህንን የጋራ መድረክ በማዘጋጀትና በማመቻቸት ታሪካዊ ሥራ ለጀመሩትና ለስኬታማነቱም ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ለሚገኙት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ያለውን አክብሮት ይገልጣል። ይልቁንም የፈጣሪያችን የእግዚአብሔርን ስም በአደባባይ በመጥራት፤ በአምላካችን ስም የማያፍሩ፣ ላመኑበት አውነት የሚመሰክሩ መልካም መሪ በመሆናቸው፤ ይህን አርአያነታቸውን ቅዱስ ሲኖዶስ ያደንቃል።

ይህ አርቆ አሳቢነታቸውና ከሕዝባቸው ጋር አብረው መቆማቸው «ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቷልና» (ዕብ. 11፥25-26) በሚለው ቃለ መጽሐፍ የተገለጠውን የሙሴን የመሪነት መርሕ መከተላቸውን ይጠቁማል። በመሆኑም የእሥራኤላውን መሪ ሙሴ ሕዝቡን ከግብጻውያን አገዛዝና እስር ነጻ እንዳወጣ ሁሉ፤ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩም ያለአግባብ በግፍ ታስረው የነበሩትን የዋልድባ ገዳም መነኮሳትን ጨምሮ በርካታ ወገኖቻችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲፈቱ ማድረጋቸው በእጅጉ የሚያስመሰግናቸው ተግባር ነው። ከዚህም ጋር አሁንም በእስር ላይ የሚገኙትንና የተለያየ ኢሰብአዊና ኢፍትሐዊ ግፍና ሰቆቃ የሚደርስባቸውን ወገኖቻችንን በአስቸኳይ እንዲፈቱ እንዲያደርጉ፣ እንዲሁም ከቀያቸው በግፍ እየተፈናቀሉ ያለ መጠለያ ቀርተው በገዛ አገራቸው ለስደትና ለእንግልት የሚዳረጉ ወገኖቻችን መከራ እንዲቆም፣ በቅርቡ ለተጀመረው የብሔራዊ መግባባት ጥረትም ከፍተኛ እቅፋት፣ እንዲሁም ለሕዝባችን ሰብአዊ መብት መገሰስ ዓይነተኛ ምክንያት የሆነው «የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ» በአፋጣኝ እንዲነሣ እንዲደረግ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንዖት ይጠይቃል።

ከዚህ በተረፈ የኢትዮጵያ አምላክ፤ እነሆ የሰጠዎትን ታላቅ ሕዝባዊ አደራና ከፍተኛ ብሔራዊ ኃላፊነት በቅንነትና በታማኝነት ተወጥው፤ በሥራ ዘመንዎ ውድ መሥዋዕትነት የተከፈለበትን ተፈላጊውን ለውጥ በማምጣት፤ ቅድስት አገራችንንና ውድ ሕዝባችንን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ እንዲችሉ፤ እንዲሁም አሁን በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት አማካይነት የተደፈረውን የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንን ሉዓላዊነት፤ በቅዱስ ፓትርያርኩና በብፁዓን አባቶች መሰደድ ምክንያት የተከፈለውን የቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሰላም አስፈላጊውን ሁኔታ በማመቻችት በዘመንዎ ለመመለስ ይረዳዎ ዘንድ፤ ልባዊ ምኞታችንና የዘወትር ጸሎታችንም ነው።

3) በቅርቡ በአገራችን በሚገኙ አንዳንድ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩና የነገዋ ኢትዮጵያ ተረካቢና ገንቢ የሆኑ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች፤ የክርስትና እምነታቸው መታወቂያ ምልክት የሆነውን «ማዕተባቸውን» እንዲያወልቁ፤ እንዲሁም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተደነገጉትን የአዋጅ አጽዋማት በአግባቡ እንዳይጾሙ፤ አላስፈላጊ ምክንያቶችን በመስጠት ከትምህርት ገበታቸው እንዲስተጓጎሉ መደረጉና ይህንን ተከትሎ በመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችን ላይ ያለአግባብ እየተደረገ ያለው ተጽእኖ፣ አላስፈላጊ የእምነት ጣልቃ ገብነት በአስቸኳይ እንዲቆምና፣ ሃይማኖታዊ መብታቸው እንዲከበር ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንኦት ያሳስባል።

ከዚህም ጋር የአገራችን ሰንደቅ ዓላማ፤ የሕዝባችንን የረጅም ዘመን ታሪክ፣ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ሕይወት የሚወክል፣ በኖኅ ቀስተ ደመና አምሳል የተዘጋጀ፤ የዕርቅና የሰላም ቃል ኪዳን ምልክት መሆኑ

ይታወቃል። አገራችን የራሷን ክብርና ማንነት እንዲሁም ብሔራዊ ሉዓላዊነት ጠብቃና አስጠብቃ ለመላው የአፍሪካ አህጉር የነጻነት ፋና ወጊ በመሆኗ፤ የሰንደቅ ዓላማችን ኅብረ ቀለማዊ መልክ የብዙ የአፍሪካ አገሮች ሰንደቅ ዓላማ መሠረት እስከመሆን መድረሱ እሙን ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት፣ ብሔራዊትና ታሪካዊት እንደመሆኗ፤ የአገራችንን ሰንደቅ ዓላማ ያለአንዳች ተጨማሪ ወይም ተለዋጭ ምልክት በኩራት ስትጠቀምበት ኖራለች። አሁንም ይህንን ጥንታዊና መጽሐፋዊ ታሪክ ተከትላ ስለምትሄድ፤ በየዘመናቱ የሚነሡ የርእዮተ ዓለም ምልክቶች የተንጸባረቁበትን ሳይሆን፤ ጥንታዊውን ሰንደቅ ዓላማ ሳይበረዝና ሳይከለስ የመጠቀም መብቷ እንዲከበር ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንኦት ይጠይቃል።

4) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱሳን ሐዋርያት በኩል ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያስተማረውን እውነተኛውንና ቀጥተኛውን ትምህርተ ሃይማኖትና ቀኖና ሐዋርያትን ጠብቆና አስጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ ይቻል ዘንድ ስብከተ ወንጌል በጥራትና በተጠናከረ መልኩ እንዲስፋፋ፣ በውጭው ዓለም ተወልደው የሚያደጉ ልጆቻችን ሃይማኖታቸውን፤ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ባህላቸውን ጠብቀውና አስጠብቀው ይኖሩ ዘንድ ልዩ ትኩረት በመስጠት የሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያው እንዲሠራ፤ ልጆቻንን ታሪካቸውን፤ ባህላቸውንና ቋንቋቸውን እንዲሁም የሕይወት ተግዳሮቶቻቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ የትምህርት፣ የጸሎትና የምክር አገልግሎት እንዲሰጥ፣ ለሕፃናትና ወጣቶች በቋንቋቸው የተጀመረው የጸሎተ ቅዳሴ አገልግሎት በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል፣ ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማሳሰቢያ ሰጥቷል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያው ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የአስተዳደር አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲሠሩ፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም ከማደራጃ መምሪያው ጋር በመተባበር እንዲሠሩ ምልዓተ ጉባኤው መመሪያ ሰጥቷል።

5) ከጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንማረው ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ከውስጥና ከውጭ የሚነሡባትን ጠላቶች በጽናት እየመከተች፤ እውነተኛውን ሃይማኖት እያጸናች ከዘመናችን ደርሳለች። በዚህ ዘመን ደግሞ በክርስትና ስም የሚንቀሳቀሱ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን ስሙን እንጂ ጌትነቱንና የባሕርይ አምላክነቱን እንዲሁም ትምህርቱን ፈጽሞ የማይከተሉ ሰዎች ተነሥተው ቤተ ክርስቲያንን በማወክና ምእመናንን በማደናገርና ግራ በማጋባት ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም፡-

ሀ) የውጭ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሰማሯቸው ቅጥረኞች አንዱ ትዝታዉ ሳሙኤል የሚባለው ግለሰብ መሆኑ ከፍሬው በሚገባ ታውቋል። ይህ ግለሰብ ከኢትዮጵያ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ወደ ሰሜን አሜሪካ ከመጣ በኋላ ዲቁናንም ሆነ ቅስናን በኢትዮጵያ ካለችው ቤተ ክርስቲያን መቀበሉን በማስረዳት፤ በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት፤ እየተጋበዘ ያገለግል እንደነበር ያታወቃል። ይሁን እንጂ ግለሰቡ ከዓመት በፊት በሥነ ምግባር ጉድለት ምክንያት ከማንኛውም አገልግሎት ታግዶ መቆየቱም ከዴንቨር፤ ኮሎራዶ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቀረበው ሪፖርት ያረጋግጣል።

ግለሰቡ በንስሐ ተመልሶ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ፈንታ የስሕተትና የክሕደት ትምህርት አራማጅ መሆኑን በመገናኛ ብዙኃን በቅርቡ ይፋ አድርጓል። ሁኔታው ያሳሰበው ቅዱስ ሲኖዶስም ግለሰቡን በአካልም ሆነ በስልክ ለማነጋገር በተደጋጋሚ ያደረገው ጥረት አልተሳካም። ይልቁንም ትዝታው ሳሙኤል ዘመኑ ያስገኘውን የማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን መድረክ በመጠቀምና ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ካሉ አካላት ጋር በመቀናጀት ትምህርተ ሃይማኖትን፣ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያምን፣ ክብረ ቅዱሳንን፣ ክብረ ክህነትንና ወ.ዘ.ተ በተመለከተ የኑፋቄ ትምህርቱን በመዝራት ላይ መሆኑ በድፍረት ከሚያሰራጫቸው የኑፋቄ ትምህርቶች ለማረጋገጥ ተችሏል።

ከዚህም ጋር ቅዱስ ሲኖዶስ በምልዓተ ጉባኤ ፊት ተገኝቶ፤ አለኝ የሚለውን ጥያቄ በግልጽ እንዲጠይቅና በድፍረት ስላስተማረው የስሕተት ትምህርትም መልስ እንዲሰጥ በደብዳቤ ቢጠራውም፤ በአካል ተገኝቶ ለማስረዳት ፈቃደኛ አልሆነም። በመሆኑም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከሥልጣነ ክህነቱ ሽሮ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት አውግዞ ለይቶታል። በመላው ዓለም የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ሁሉ ይልቁንም የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ከዚህ ግለሰብ የክህደት ትምህርትና አፍራሽ ተልእኮ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንዖት ያስጠነቅቃል። በመሠረቱ መፍቀሬ ሰብእ የሆነው እግዚአብሔር የሰውን መዳኑን እንጂ ጥፋቱን አይወድምና፤ ትዝታው ሳሙኤል ጥፋቱን አምኖ፣ ስሕተቱን ተረድቶ፣ በንስሐ ተጸጽቶ ለመመለስ እንዲችል እግዚአብሔር ቀና ልቡናና አስተዋይ አእምሮ እንዲሰጠው እየጸለይን፤ ተጸጽቶ ሲመለስም በንስሐ ለመቀበል የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደጅ ዘወትር ክፍት መሆኑን እናሳውቃለን።

ለ) ዘርፌ ከበደ የተባለችው ግለሰብም እንዲሁ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ወደ ሰሜን አሜሪካ ከመጣች በኋላ በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወረች በመዝሙር ታገለግል እንደ ነበር ይታወቃል። ይሁን እንጂ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና ሥርዓት ውጭ የሆነ የኑፋቄ ትምህርት መከተል በመጀመሯ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትና መምህራን ካህናት በተደጋጋሚ ቢመክሯትም አባታዊ ምክራቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኗ፣ የስሕተት ትምህርት አራማጅ በመሆኗ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት አውግዞ ለይቷታል። በመሆኑም ምእመናን ይልቁንም የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ከዘርፌ ከበደም ሆነ ከትዝታው ሳሙኤል የክህደት ትምህርትና የጥፋት ተልእኮ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንዖት ያሳስባል። በአንጻሩ ደግሞ በየጊዜው ለሚነሱ ሃይማኖታዊ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ የሚሰጥና ምእመናንን በኦርቶዶክሳዊት እምነቱ የሚያጸና ትምህርት በሊቃውንት ጉባኤ ኃላፊነት በተቀናጀ መልኩ በጉባኤና በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ተጠናክሮ እንዲሰጥ መመሪያ አስተላልፏል። ለዚህ ሐዋርያዊ ተልእኮ መሳካት አብያተ ክርስቲያናት ሁለንተናዊ ትብብር እንዲያደርጉ መልእክቱን ያስተላልፋል።

6) ከአለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ወዲህ በአገራችን የተከሰተውን የሥርዓተ መንግሥት ለውጥ ተከትሎ ሕጋዊውና አራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የሆኑት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስ ከሐዋርያዊ መንበራቸው በግፍ በመሰደዳቸው ምክንያት በተፈጠው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ልዩነት ምክንያት፤ ችግሩ በዕርቀ ሰላም ውይይት ተፈትቶ የቀደመው የቤተ

ክርስቲያናችን አንድነትና ሰላም እስኪመለስ ድረስ «በገለልተኛነት» የቆያችሁ አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ በአገር ቤት በሚገኙት አባቶች ሥር የምትተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ፤ እነሆ ወቅቱ ከምንጊዜውም በላይ ከመራራቅ ይልቅ መቀራረብን፣ ከመለያየት ይልቅ አብሮነትን፣ ጎራ ለይቶ ከመነቃቀፍ ይልቅ መመካከርን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን፣ በውድ አገራችንና ሕዝባችን አንድነት ላይ አብራችሁን እንድትሠሩ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያስተላልፋል።

7) በመላው ዓለም የምትገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በሙሉ፤ እነሆ ለቅድስት አገራችን ኢትዮጵያ ህልውና መሠረት፣ ለሕዝቧም አንድነት ባለውለታና ለሕያውና አኩሪው ታሪካችን ታማኝ ጠባቂ ለሆነችው ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያናችን አንድነትና ሰላም መሳካት ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ በያላችሁበት የበኩላችሁን አስተዋጽዖ እንድታደርጉ፣ቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ ጥሪውን ያቀርባል። የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችሁንም እምነትና ሥርዓት ጠብቃችሁ እንድታስጠብቁ፣ ከዘመኑ የሐሰት ነቢያት ትምህርትና ምትሐታዊ አሠራርም ራሳችሁንና ልጆቻሁን በሚገባ እንድትጠብቁ ሐዋርያዊ አደራውን ያስተላልፋል።

በመጨረሻም 47ኛውን የርክበ ካህናት ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ከግንቦት 1-3 ቀን 2010 ዓ.ም (May 9-11, 2018) በተሳካ ሁኔታ በማስተናገድ የደከሙትን፣ ለጉባኤው ውጤታማነት በእጅጉ የተባበሩትን በካሊፎርኒያ፤ ሳንሆዜ የመካነ ራማ ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ካቴድራል ማኅበረ ካህናትና ምእመናን፤ የአስተዳደር ቦርድና የሰ/ት/ቤት አባላትን በማመስገንና በመባረክ ጉባኤው በጸሎት ተፈጽሟል።

Abba Michael Archbishop Vice
Secretary of the Holy Synod